# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞክራሲያ ቁጥር 38 ቁጥር 4** **የካቲት 2005 ዓ.ም**


## *የካቲት 1966--የካቲት 2005*

## *የካቲት ይናገር፣ የካቲት ይመስክር!!*

> *" የካቲት አልፎ ሌላ የካቲት ሲተካ በየካቲት 66 በንብረት ተነስቶ ጊዜ ያለፈበትንና ሕዝብን የበደለ ሥርዓት ያስወገደውን ትውልድ ስናስታውስ ከሁሉም በፊትና በላይ ፊታችን ተደቅኖ የሚታየን ያልተገላበጠ ማረፉንና ያልታገለ ደግሞ ለቀንበር፣ ለባርነት፣ ለብዝበዛና ለማያባራ ጭቆና መዳረጉን ነው ። ዛሬ ደግሞ በስግብግብና በአረመኔነት የሚታወቀውን የአገዛዝ ሥርዓት ከማስፈኑ በተጨማሪ ሀገርን ለማጥፋት አልሞ የተነሳና ይህንንም እኩይ ተልዕኮ ከግብ ለማድረስ እየጣረ ያለው ቡድን በሥልጣን ላይ በመሆኑ የየካቲቱ 66 መልዕክት ከነጎድጓድ በላይ እየጮሐ ለሀገር አድን ትግል ይጠራናል። "* (ዴሞክራሲያ የካቲት 1994)

በኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ውጣ ውረድ፣ ድል ሽንፈት፡ ሐዘን ፈንጠዚያ፣ ሽብር ሰላም ሲፈራረቁ የታየው የመቶ ሳይሆን የሺ አመታት ሂደት ውስጥ ታላቅና ክቡር ቦታ የያዘው የየካቲት አብዮት ከተከሰተ 39 ዓመታትን አስቆጠረ ። ትላንትን እንዳለ ዛሬ መድገም ባይቻልም ለአብዮቱ መሰረት የሆኑ የሕዝብ ብሶቶችና ጥያቄዎች ዛሬም አሉና የየካቲቱ ትግል በተሻለ ውጤት ታጅቦ የማይፈነዳበት ምክንያት የለም ። ሕዝብ በጋራ ተነስቶ ስርዓቱን ማቸነፉ ጿጋ ሆኖ ድሉን ሊጠብቅ ሊያስከብር አለመቻሉ ደግሞ እስከዛሬ የሚያቃጥለን ድክመት ነው ። የካቲት 66ን ስናስታውስ ዛሬ ከሁሉም በፊትና በላይ ያን የትግል መንፈስና ወኔ መድገም አለመቻላችን ብቻ ሳይሆን የዚያን ታሪካዊ ወቅት ቅርስ የሚያጥላሉና የሚያንኳስሱ መብዛታቸውን ነው ። የሀገርና የሕዝብን ታሪክ ቅራሪ ማድረጉ -- አሳፋሪ ቢሆንም--ለወያኔ ብቻ የተተወ ወራዳ ተልዕኮ አይደለም ። እንደ አይጠ መጎጥ የክፉ፣ነጋ ጠባ ታሪክን እየነከሱና እየቦጨቁ ተከታዩን ትውልድ የተበላሸ ግንዛቤን ለማስጨበጥ የተራወጡና የሚሯሯጡ መኖራቸው ደግሞ የሚታወቅና ከቶም መረሳት የሌለበት ነው ።

ዴሞክራሲያ የኢሕአፓ ልሣን መሆኗን ያበሰረችው በየካቲት መባቻ ወቅት ነበር። የኢትዮጵያ አየር የጭቁኖችን ብሶት አርግዞ፣ የአፄው ፊዩዳላዊ አገዛዝም "ሞ አንበሳ ዘዕመ ነገደ ይሁዳ ሥዩመ እግዚአብሄር ዘኢትዩጵያ" የሚል ከምድራዊም ሆነ ከሰማያዊ ህይወት ያልተገናዘበ፣ ዘውዳዊ ትራስ ተንተርሶ ለዘመናት ከተኛበት የዕንቅልፍ ህይወት ሳይነቃ፣ የየካቲት ሕዝባዊ አመፅ የሀገሪቱን ፓለቲካዊ

መልከዓ ምድር አጥለቀለቀው። የአመፅ ወላፈን በዚህም በዛም መቀጣጠሉን ተያያዘው። የየካቲት አብዮት፤ ህልውናውን፣ ውስጣዊ ባህሪውን፣ መልዕክቶቹን ጭምር ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ አስተጋባ። አዲስ ክስተት፣ አዲስና ሥርነቀል ህይወት የሚጠይቅ አብዩት በሀገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ እራሱን ዕውን አደረገ። እልፍ አእላፍ ሕዝብ የየካቲቱ አብዮት ባነሳቸው መሪ ጥያቄዎች ዙሪያ ተሰባሰበ፣ የየካቲትን ስንደቅም አነገበ ። የየካቲት አብዩት ሕዝባችን ባለፉት የታሪክ ዘመናት በጋራ ያፈራቸውን ባለብዙ መልክ ትስስሮች፣ ታሪካዊና ባህላዊ ግንኙነቶች፣ በነዚህም ላይ ተመርኩዞ እውን ሊሆን የቻለውን ሕዝባዊ አንድነትና አገራዊ ሉዓላዊነት አልተፈታተነም፣ በጥቅሉም ጥላሸት ቀብቶ አላለፈም። የየካቲትን አብዩት ልዩና ሕዛባዊ የሚደረገውም ሕዝብ በጋራ ለሠራቸውና ላፈራቸው ትላልቅ ክስተቶች በአጠቃላይ ክብር ሰጥቶ፤ የጐደሉትን ግን በሚገባ ጠቁሞ፣ አጠቃላይ ሕዝቡን በዘላቂና ቋሚ የሙብትና የሁለገብ እኩልነት ዐበይት ጥያቄዎች ዙሪያ ለማሰባሰብ መቻሉም ነው።

የካቲት 66 ግብታዊ ነበር፤ በድንገት ፈነዳ ቢባልም ሀቀኛ ምርምር ግን ለዓመታት የተካሄዱ ሕዝባዊ ትግሎች ውጤት መሆኑን ያሳያል ። አብዮትን ጭቁን ሕዝቦች የሚታግሉለትና የሚፈልጉት--የሚጠብቁት ነው--ቢጠበቅም ግን የፍንዳታው ጊዜ ድንገተኛነትን መያዙ የማይቀር ሆኖ ይግኛል ። የካቲት 66 የደም የመስዋዕትነት ውጤት ነው ። ከጥቁር አንበሶች ጀምሮ እነ በላይ ዘለቀንና ስንቶቹን የተበደሉ የተሰዉ አርበኞችን ጨምሮ፤ ቢያንስ ሶስት መፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎችን ይዞ፤ የእነ ደጃች ታከለን ትግል ዘክሮ በየቦታው የፈነዱ የአርሶ አደሮችን አመጾችና የላባአደሩንም ትግሎችና አድማዎች አቅፎና በተለይም ከዓመት ዓመት ሳያቋርጥ የተካሄደውን የተማሪዎች ትግልና መስዋዕትነትን መሰረት አድርጎ፤ ምሬት በምሬት እየተደጋገፈ ግፉ ሞልቶ ሲፈስ የፈነዳ ነው ። ግብታዊ የሚያሰኘው ካለ የነበሩ ሀይሎች (ለምሳሌ ኢሕአፓ የተመሰረተው በ 1964 ነበር) ባልጠበቁበት ጊዜ ነበር አብዮቱ የፈነዳው ። ይህን አጋጣሚ በማፋፋም ግን ኢሕአፓም የመሪነቱን ሚና ለመያዝ አቅም ባይኖረውም ታሪክ ሊረሳ የማይችለው ሚናን ተጫውቷል ። ዛሬ ይህን ማድረግ ባለመቻሉ የለውጥ አዋላጅ ሊሆን የሚችል ሕዝባዊና ያመረረ ትግል (ለምሳሌ የሙስሊም ኢትዮጵያውያን ቀጣይ ትግልን ያነሷል) ከሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ባለማግኘቱ ትግሉ ስርዓቱን አስወጋጅ ሊሆን ገና አልቻለም ። ገዢ ነኝ ያለው ቡድንም ውስጡ እየተፍረከረከ ቢገኝም ይህን ቀውስ አብዮት አዋላጅ ለማድረግ ገና አልተቻለም። ይህ ደግሞ ምን ጎደለ፤ ድክመታችን የት ላይ ነው፤ ትውልድስ ሀላፊነቱን መሸከም አቃተው ወይ ብሎ መመርመሩን ተገቢና ግዳጅም ያደርገዋል ።

ወያኔ ለሥልጣን በባዕዳን እርዳታ ከበቃ ጀምሮ ሕዝባዊ ትግሎች በየአቅጣጫው ብቅ ብቅ ብለዋል ። ዜጎች አላንቀላፉም ። የተዘረጋባቸውን ጋሬጣ እያስወገዱ ታግለዋል፤ ተሰውተዋልም ። ዘመኑ አብዷል፤ ወኔ ጠፍቷል፤ ሆድ አቸንፏል በሚል ይህ ብዙ የሚወቀሰውም ትውልድ ቢሆን የሽንፈትን እንቅልፍ አላንቀላፋም ። ምናልባትም ዋናው ጥፋት ከአታጋዮቹ ድክመትና ከስርዓቱም ከፋፋይነትና መሰሪነት

ሊሆን የሚችል መሆኑን ማጤን ማመን ተገቢ ይሆናል ። በ 1966 ዋዜማ በአዲስ አበባ የነበረው ሁኔታ ሊያደራጁ ለተነሱ ለነኢሕአፓ ዓይነቶቹ መቶ በመቶ አመርቂና አበረታች አልነበረም ። ግን ይህንን ድክመት አቸንፎ ለሀገሩ ለወገኑ በድፍረት በወኔ ሊሰዋ የሚችልን ትውልድ ኢሕአፓ ሊያፈራ ችሏል ። ዛሬም ይቻላል ። መደረግ ያለበትን ማድረጉ፤ ወኔና ድፍረቱ፤ ሀገርን ማስቀደሙ፤ ለጠላት አለመንበርከኩ፤ለመስዋዕትነት ዝግጁነት ካሉና ከተከሰቱ የየካቲት 66ቱ እንቅስቃሴ በአዲስ ሊከሰትና የሕዝብን ድል እውን ለማድረግ ይቻላል ። የየካቲት 66 አንዱና ወሳኝ ትምህርቱ ግቡን ማወቁ ነው ። በየፌርማታው ትግሉን ማጅራት ለመምታት የታለሙ የጥገና ለውጥ አይነት ማጠፊያዎችን ሕዝብ አልተቀበለም--ትግሉን ገፋበት እንጂ ። ሠራተኛው በጠቅላላ የስራ ማቆም አድማ የእንዳልካቸው መኮንንን አከሻፊ ሙከራ አቸንፎታል ። አብዮቱ ወደ ሥርዓት ለውጥ በማምራቱና በዚህም በማምረሩ ስርዓቱ ተወግዷል ። ሕዝብ ግን ድሉን በታጠቁ መኮንኖች ተነጥቋል። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን የየካቲት 66 ምሳሌነቱ የሕዝብ ቆራጥና የተባበረ ትግል ምን ያህል ሀገርን ሊያድን እንደሚችል ማሳየቱ ነው ። የነበረውንና የተከተለውን ሁኔታ በሚመለከት በየካቲት 1993 ዴሞክራሲያ የሚከተለው ሰፍሮ ነበር፤

> *"እንደ ሕዝብ አልታደልንም፤ የተረገምን የካም ልጆች ነንና ብለን ፤ ዕጣችን ነው ያልነውን ተቀብለን፤ ራሳችንን አቅም ነስተን፤ለጨለምተኝነት ተዳርገን መጨረሻችንን የምንጠብቅ ግን አይደለንም። ሕይወታችንን ለመለወጥና የራሳችንን ማደሪያና ዕጣ ለመወሰን አቅዋም ችሎታም ያለን ፍጡሮች ነን ብለን ከተነሳን ከምንመኘው ግብ ለመድረስ የሚያግደን ሀይል ሊኖር እንደማይችል እንገነዘባለን ፡፤ በየካቲት 66 ለውጥ ፈልጎ የተነሳውና የታገለው ሕዝብ ድልን የተቀማው በበቂ ባለመደራጀቱነ ድሉን ማስከበሪያ ክንዱን ባልማፈርጠሙ መሆኑን ዛሬ በግልጽ የምናየው ነው ። ጨፍጫፊው መንግሥት ወርቅ ትውልድን በመንገድ ዘርሮ ግዳይ እንደጣለ ጀግና ሲፎክር ሀግሪቷም ጎህ ቀዶ ብርሃን ሳይፈነጥቅባት በጨለማ ተውጣ መቀመቅ የምትወርድበት መንገድ ተጠረገ ። "ኢትዮጵያ ሀገሬ ተስፋዬም ነሽ ክብሬ" ብለው የተነሱትንም በመምተሩ ኢትዮጵያን ጠላቴ ብለው በብሔረሰብ ሽፋን ጠባብና አጥፊ ዓላማን የገፉት ጸረ ኢትዮጵያ ክፍሎች ሌላ መንገድ ተጠረገላቸው ። ይህችን ነጻነቷንና አንድነቷን አስከብራ የቆየችን ሀገር ለማንበርከክ የቅርብም የሩቅም ጠላቶች ለዘመናት ሲጥሩ ግን ሳይሳካላቸው ኖረው ነበር ። የእነ ወያኔ ዓይነት ከፋፋይና አጥፊ ቡድኖች መፈልፈል ከሰማይ የወረደ መና ሆነላቸው ። ፈርንጆም አረቡም ከሀገር አጥፊዎች ጎን ተሰለፍ ። ጠላት ጠላት መሆኑ የሚጠበቅ ሆኖ ሳለ የሚያሳዝነው ክስተት ግን ሀገሩን መጠበቅ ያለበት ዘጋ ደግሞ በሰብብ አስባቡ ተዘናግቶ፤ተከፋፍሎ በአጥፊዎቹም የአንድ ጠዋት "ኢትዮጵያዊ" ነን ባይነት ተደናግሮ ለሀገር ከሚታገሉት ጎን በሚገባ ለመሰለፍና ለመቆም አልቻለም ። ትውልድ አጥፊው የደርግ ስርዓት ለሀገር አጥፊው የወያኔ ቡድን ምንጣፍ ዘርግቶና መንገድ ደልድሎ ተንኮታኮተ" ።*

በየካቲት 66 ሕዝብ ያነሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ዛሬም ምላሽ አላገኙም። መሰረታዊው መሬት ለአራሹ ጥያቄ--ከአጼው ዘመን ጀምሮ የትግል ዕምብርት ምላሽ አልባ ሆነ አለ ። የአርሶ አደሩ የሆነው የሕዝብ ጥያቄ--ላቡንና የተሻለ ቀን ተስፋውን የሚያፈስበት መሬት የራሱ አይደለም--የወያኔ ነው በመንግስት ሽፋን ። መሬት ለአራሹ፤ ዴሞክራሲ አለገደብ ለጭቁኑ፤ ሉዓላዊነት ለኢትዮጵያ፤ ሙብት ለላባደሩ፤ ወዘተ ሁሉም የያኔ ጥያቄዎች ዛሬም መልስ አላገኙም። ይህም በመሆኑ ትግሉ መቀጠሉ የግድ መሆኑ አልቀረም

። ትግሉ እንዴት ይቀጥላል የሚለው ጥያቄ ግን የዛሬን መልስ የሚጠይቅ ነው --ጊዜና ሁኔታን ለውጥን የሚያጤን ነውና ። በየካቲት 66 የነበረው ተጨባጭ ሁኔታ በየካትቲ 2005 ይኖራል ብሎ መጠበቅ አይቻልም ። ይሁን እንጅ ግን ለአብዮቱ መፈንዳት ምክንያት የሆኑት ሁኔታዎች ዛሬም። በደርግም በወያኔም ምላሽን አላገኙምና ። ትግል ቀጣይ እንዲሆን ቀጣይነቱን የግድ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መኖር አለባቸው ። በቅድሚያ አታጋይ መፈክሮችና ጥያቄዎች ምላሽ አልባ ሆነው መገኘታቸው ይነሳል ። በመሆኑም የየካቲት አብዮት ወቅታዊ ይዞታውን ተላብሶ የማይፈነዳበት ምንም ምክንያት የለም።

ታታሪና ፈጣሪ የሆነው ሕዝብ ለዘመናት የጭቆናን ቀንበር ተሸክሞ፣ አፉ ተሸብቦ እንዲኖር የተገደደበት፣ መብትና ዘላቂ ሠላምን ተነፍጐ በፍትዕና ርትዕ ጥማት እየተጐሳቆለ ዘመናት ያለፉበት መሆኑም ሊካድ የማይቻል የታሪኩ ሌለኛው ገፅታ ነው። ኢትዮጵያ፣ ሠራተኛው በሥራው መጠን የሚከፈለው ሳይሆን፣ ላቡን ባፈሰሰ ቁጥር የጭቆና ሠንሠለቱ እያደር የሚወጠርበት፣ በነፃ የመደራጀቱ መብቱ በገዢዎች ተመንና ፍላጎት የሚለካበት ሁኔታ ውስጥ ተዘፍቆ ኖሯል። የሃይማኖቶች እኩልነትም የተከበረባት አገርም አልነበረችም። የሴቶችም እኩልነት በሕግ ያልተከበረ ብቻ ሳይሆን፣ በወንድ ትምክተኝነትና የበላይነት እንዲሁም በከፋ ባህላዊ ተፅዕኖ ሥር የወደቀበት የመጥፎ አስተዳደር መግለጫ እንደሆነ ዘመናት አልፈዋል። የመምህራን፣ የተማሪዎች፣ የብዙሃን የህብረተሰቡ ክፍሎች መብትና ጥቅም ደብዛቸው ጠፍቷል። አርሶ አደሩ የመሬቱ ባለቤትነት ፀጋው ተገፎ ለዘመናት በአገር በቀል ፊዩዳሎችና የግፍ አገዛዝ አባወራዎች ለፍቶ መና ህይወት እንዲገፋ ተፈርዶበትል ---ወዘተ።

የየካቲት አብዮት እነዚህን ሁሉ አስተባብሮና አስተሳስሮ ያስነሳ ሥርነቀልና አገር አቀፍ፣ የዘመናት መካተት ሊሽረው ያልቻለ ህዝባዊና አገራዊ አብዮት ነው። የየካቲቱ ህዝባዊ አመፅ ካነሳቸው በርካታ ጥያቄዎች ጥቂቶቹ:-

ሀ) መሬት ላራሹ ይሁን

ለ) የዲሞክራሲ ጥያቄ ካለገደብ ይከበር

ሐ) የፍትዕና ርትዕ እንዲሁም የሰብዓዊ መብቶች ይከበሩ፣

መ) መብት ለላባደሩ ይሰጥ፤

ሠ) መንግሥትና ሃይማኖት ይለይ፤ መንግሥት በሃይማኖት/ሃይማኖት በመንግሥት ጣልቃ አይግባ

ረ) የዜጎች እኩልነት፤ የብሔሮች እኩልነት ይረጋገጥ

መ) ሕዝባዊ መንግሥት ይመሥረት

ሠ) በህዝብ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ ላዓላዊነት እውን ይሁን ---ወዘተ። እስከዛሬ ድረስ አድሃሪና መብት ገፋፊ ፀረ ሕዝብ አገዛዞች ተቀያየሩ እንጂ ከላይ የተዘረዘሩት የየካቲት ሕዝባዊ ትግል ያነሳቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች አንዳቸውም አልተመለሱም። በሌላኛውም አኳያ ደግሞ እነዚህ ስርነቀል

የሆኑ ህዝባዊ ጥያቄዎች ያዘሉትን ቁም ነገርና የሰነዘሩትን የመፍትሄ ሀሳብ ሊተካ የሚችል አማራጭ አልተገኘም። ሊገኝም የሚታሰብ አይሆንም። በሌላ በኩል ግን እነዚህ የየካቲቱ ህዝባዊ አብዮት ያነሳቸው ጥያቄዎች ይበልጥ ስር እየሰደዱና በብዙሃን ሕዝብ ውስጥ ግንዛቤ እያገኙ ለጨቋኝ ገዢዎች አልሙች አሉ እንጂ፣ የአድህሮት ሃይላት እንደተመኙት ተነው የሚጠፉ አልሆኑም።

የ1966 የየካቲት አብዮት ዛሬም ህያው ነው ስንል ይህን መሰል ባህሪውን ስለምንገነዘብም ነው። ላለፉት አርባ ዓመታት የተካሄደው የሀሰት ክምርና ክስ፣ የየካቲቱ ህዝባዊ አመፅ ያዘላቸውን ቁም ነገሮች አልናደም። የጥያቄዎቹንም ዛሬም ህያው ሆኖ መቀጠል አልሻረም። *የካቲት ዛሬም እንደወትሮው እያታገለና እየታገለም ነው።* የየካቲቱ ሕዝባዊ አብዩት "ሀ" ብሎ ጉዞውን ሲጀምር፣ የትኛው ወገንና እነማን ከህዝቡ ጥያቄዎች ዙሪያ ተሰባስበው ለህዝብ መብትና በእኩልነት ላይ ለተመሠረተ ሀገራዊ ሉዓላዊነት ተገቢውን መስዋዕትነት እየከፈሉ ትግሉን እንደቀጠሉ፣ የትኞቹስ ከአስከፊ *ሥርዓቶ*ችና ከጠላት *ጋ*ር እንደወገኑ፣ የትኞቹስ በትግሉ ሂደት ተንጠባጥበው እንደቀሩ ጠንቅቆ ያውቃል። የካቲት ያነሳቸው ጥያቄዎች የትግል መርሆ ብቻ ሳይሆኑ የትግሉ ሂደትም ምስክሮች ናቸው። ይህ ባይሆንማ ኖሮ *ታሪክ የቆርጦ ቀጣዮችና የቃለ አባዮች ወመዘክር ሆኖ በቀረ ነበር።* ይህ ሊሆን ግን ከቶውንም አልተቻለም። ቀን ባለፈ ቁጥር እውነት እየፈካ ወጣ እንጂ አልደበዘዘም። ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት፣ ከዛም በኋላ በየትግሉ የሂደት ደረጃ ከየካቲት *ጋ*ር ወግነን፣ ህይወትን ጭምር እየገበርን ያልነው ሁሉ እውነት መሆኑ ተረጋገጠ እንጂ በሃሰትነት አልተሻሩም።

የየካቲቱን አብዮት በሚገባና ጠለቅ ባለ መንገድ ከመረመርነው ደግሞ እያታገለና ምስክርነቱንም እየሰጠ ብቻ አለማለፉንም መገንዘብ የሚከብድ አይሆንም። የየካቲት ዋነኛውና ውስጣዊ ባህሪው *እየታገለም መኖሩና እየቀጠለም መሆኑም ጭምር ነው።* የካቲት ያነሳቸው ጥያቄዎች አለመመለስ ለዘውዳዊው አገዛዝ መውደቅ ዋነኛው ምክንያቶች ናቸው። ጭራውን ቆልፎ ለሶሻየት ህብረት ላደረውና አንድ ትውልድ በመምተር ሀገሪቷን ለወያኔ አመቻችቶ ለፈረጠጠው ወታደራዊ አምባገነን ቡድንም ሽንፈት ዋነኛው ምክንያት በየካቲት አብዮት የተነሱት ጥያቄዎች አለመመለስ ነው። የየካቲትን ሂደት ቆልምሞ፣ የየካቲትን ጥያቄዎች አፍኖ የህዝብን ልብ ማግኘት አይቻልም። የጠመንጃ ብዛት፣ አምባገነናዊ ትምክህትና ትዕቢት እንዲሁም ገደብ የለሽ ውሸት የካቲት ያነሳቸውን ጥያቄዎች የሚመልሱ አልሆኑም። ወደፊትም ጨርሶ ሊመልሱ አይችሉም። ዛሬም የወያኔ ዘረኛና ጎሰኛ፣ ፀረ መብትና ፀረ ኢትዮጵያዊው ቡድን ተጣቦና ከህዝብ ተነጥሎ ያለው የካቲት ካነሳቸው *ሥር*ነቀል ጥያቄዎች *ጋ*ር በገጠመው ግብግብ ነው። የየካቲት እውነት ወያኔንም እያንገዳገደው ነው። እነዚህ ሁሉ በግንዛቤ ሲወሰዱ የየካቲት ዛሬም ፀረ መብትና ፀረ ሰላም የሆኑትን ሁሉ እየታገለ ያለ መሆኑ ግልፅ ነው።

በአጠቃላይ የአገራችንና የህዝባችን ሁኔታ ሲገመገም ዘረኛውና ጐጠኛው የወያኔ ቡድን ኢትዮጵያን ለመበዝበዝና የዜጐቿን መብት ረግጦ ለመግዛት ብቻ ሳይሆን ሕዝቧን ከፈፍሎና አዳክሞ አገሪቷን በታትኖ

ለመሄድ ዕቅዱንም እያጣደፈ ነው። በሌለኛው አኳያ ደግሞ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ የጀግናና የእውነተኛ ልጆቹ ያለህ እያሉን ናቸው። ከዚህ እውነታ ስንነሳ ዋነኛውና የማይታረቀው ቅራኔ፣ በአንድ በኩል በኢትዮጵያ ሕዝብና ከሱጋር በወገኑ ሀቀኛ ድርጅቶችና ልጆቹ፣ በሌላው በኩል ደግሞ በዘረኛውና ጉጠኛው ፀረ መብትና ፀረ ኢትዮጵያ የጥፋት መልክተኛ ቡድንና ግብረአበሮቹ መሃል ያለው ቅራኔ መሆኑ ግልፅ ነው። ሌላው ሁሉ በመለስተኛ ደረጃ ሊታይ የሚገባውና የሚፈረጅም የቅራኔ አይነት ነው።

ስለዚህ ይህን በመሰለ አስከፊ ጊዜ ምን መደረግ አለበት የሚል ጥያቄ ሲነሳ፣ በዚህ መሠረታዊ ቅራኔና የኃይል አሰላለፍ ላይ የተመሠረተ ሕዝባዊ ትግል/አመጽ ማስፈለጉ ሊዘለል የማይችል ሃቅ ነው

*የየካቲት አብዮት እንደተዳፈነ እሣት የሚወሰድ፣ እንደ እሣተ ገሞራም ኃይሉን እያጠራቀመ ለጠላቶቹ ሁሉ መቅሰፍት የሚሆን ህዝባዊ ኃይል ነው፡፡* ምን ጊዜም ሕዝብ አቸናፊ ነው የሚባለውም ከዚህ አብዮታዊና ሕዝባዊ ባህሪው በመነሳት ነው። ለዚህም ነው፣ የካቲት ዛሬም እያታገለም እየታገለም ነው ስንል እውነት ሆኖ የሚገኘው።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

እናቸንፋለን !!!